# ሽርሞ ለሽርሞ

## ክፍል ሁለት--- ትግል በአንቀልባ

<u>የሶፋ ዘመቻ</u>

<u>ሀማ ቱማ</u>

ቃላት ጥይት ሆነው
    ምላስም ጠመንጃ
ጉድብ ሶፋ ሆኖ
    ኮኛኩም የደም ጎርፍ
መለፍለፍ መተቸት ማለምን ተክቶ
        ምላሽ ተኩስም ጠፍቶ
መንጣጣት በርክቶ፡፡
ጀግናው በረከተ ፋኖው ከፋኝ ባዩ
            የቁጭ ስኳድ በዛ
የርቀት አዋጊ
የወሬ አርበኛ
የምላስ ማራኪ፡፡
ጠላት ልቡ ሞላ
ገጠምኩህ የሚለው በሩቅ ስለተኛ ፡፡
ከወሬ ባሻገር ከሶፋ ዘመቻ
ትግል ስለተፈራ፡፡
የሚነካው ጠፍቶ ጠላት ልቡ ሞላ፡፡